# ጉድ በል ሃበሻ!ለመሆኑ አቦይ ስብሃት እኚህ ነበሩ?

ደመካሽ በቀለ (satenaw2000@gmail.com)

እስከቅርብ ጊዜ ድረስ አቦይ ስብሃት ነጋን ፍጹም በድምጽ ሰምቻቸዉ አላዉቅም ነበር። በድምጽ አለመስማት ብቻም ሳይሆን ድሮ ድሮ ሰዉየዉ በአስተሳሰባቸዉና በአመለካከታቸዉ ምን ሊሆኑ ይችላሉ? በሚል ለራሴ ላቀረብሁት ጥያቄ ሰጥቼ የነበረዉ ምላሽና በምናቤም ለማስቀመጥ የሞከርሁዋቸዉ 'እሳቸዉ' በፍጹም በፍጹም እንዲህ እንዳሁኑ በእዉነተኛዉ ዓለም እንዳሉትና በጆሮየ እንዳዳመጥሁዋቸዉ አቦይ 'ስበላ ነጋ' (አቦይ 'ስጠጣ ነጋ') አይነትን አልነበረም።

በአማርኛው የአሜሪካ ሬዲዮ ድምጽ ፕሮግራም ከአቶ አዲሱ ጋር ባደረጉት ቃለምልልስ አቦይ 'ስበላ ነጋ'ን ጥሩ አድርጌ ደጋግሜ አዳመጥሁዋቸዉ፡ ። በነገራችን ላይ የአዲሱ የጋዜጠኛነት ብቃት (ምንም እንኩዋን ከዚያች ዕለት በፊትም የማደንቀዉ ጋዜጠኛ ቢሆንም) እንደዚያች ዕለት የተለየ ስሜት ሰጥቶኝ አያዉቅም። የተፈጠረብኝ የተለየ ስሜት ለአቦይ 'ስበላ ነጋ' ባቀረባቸዉ ጥያቄዎች ምክንያት ሳይሆን ለጥያቄዎቹ ከሰዉየዉ ይሰጥ ለነበረዉ ምላሽ አቶ አዲሱ የነበረዉ በትዕግስት የማዳመጥ ብቃት፡ የዉስጥ ስሜትን የመቆጣጠር ችሎታ፡ እንዲሁም ለእንዲህ አይነቱ ተራና የወረዱ ሰዉ የነበረዉ አክብሮት ናቸዉ። በአቶ አዲሱ ቦታ እራሴን አስቀምጬ ሳስበዉ ግን... ይቅር...አለመናገር የሚሻል ይመስለኛል። በዚያች ዕለት እሳቸዉን በማዳመጤ የተፈጠረብኝ አሳፋሪ ስሜት በዚያዉ ሊገታ በቻለ ኖሮ ምንኛ መልካም ነበር? ከዚያን ዕለት በሁዋላ... በእዉነት ነዉ የምላችሁ፡- ይህች አገር በእነኝህ አይነት ሰዎች፡ አይደለም ለወራትና ለዓመታት፡ ለአንድ ቀንም ቢሆን 'መመራቱዋ' ልቤን በብርቱ ማድማት ጀምሩዋል።

በእርግጥ የወያኔ መሪዎችና ጭፍሮቻቸው ይዘዉት ለተነሱት አገር አጥፊ ሰይጣናዊ ዓላማ ተግባራዊነት ሲፈጽሙ ለቆዩዋቸዉና እየፈጸሙ ላሉዋቸዉ አሳፋሪ ተግባራት አዲስ አይደለሁም፡ ልሆንም አልችልም። በተለይም 'መሪዎቻችን' ምን ያህል ለከት የለሾች እንደሆኑና በምንም አይነት መመዘኛ የሰብዓዊ ፍጡር ባህሪን የተላበሱ እንዳልሆኑ በሚገባ አዉቃለሁ የሚል እምነት አለኝ። ነገር ግን......ነገር ግን..... ይህች አገር በእነኝህ አይነት ተራ፡ ከተራም ተራ በሆኑ የመንደር ጥርቅሞች እጅ መዉደቁዋ እንዲህ እንደአሁኑ ከመዘግነን አልፎ አንቀጥቅጦኝና አሳስቦኝ አያዉቅም።

ወዳጆቼ አስቡት! እንግዲህ ኢህአዴግን በተለይም ለጠቅላይ ሚንስትራችን ቅርበት እንዳላቸዉ የሚነገርላቸዉና አቶ መለስን (ጋሼ አቤን) በፈለጉት አቅጣጫ እንደሚያሽከረክሩ የሚነገርላቸዉ፡ ብዙ የተባለላቸዉ አቦይ ስብሃት እኚህ ናቸዉ ማለት ነዉ። ታዲያ አቦይ እንዲህ ከሆኑ ኢህአዴግ ስንት ሌሎች የአቦይ ስብሃት አይነቶችና ከእሳቸዉም በታች በአስተሳሰባቸዉ የወረዱ ግለሰቦች ይኖሩት ይሆን? አይ አለመታደል! ይህች አገር ያፈራቻቸዉና እድሉን ቢያገኙ ስንት ተዓምር ሊያሳዩ የሚችሉ በርካታ ዜጎች በእስርና በስደት እየተንገላቱ ባለበት ሁኔታ አገራችን በእንዲህ አይነት አደገኛ ቦዘኔዎች እጅ ትውደቅ?

በዚች አነስተኛ ጽሁፌ ከአቶ አዲሱ ለአቦይ 'ስበላ ነጋ' በቀረቡት ጥያቄዎችና አቦይም በሰጡዋቸዉ መልሶች ዙሪያ የምለዉ ነገር አይኖረኝም። ምንስ ሊባል ይችላል? እንኩዋን የተባለዉን በመድገም አስተያየት መስጠት ይቅርና ቀደም ብሎ አቦይ እንዲህ አይነት 'ሰው' መሆናቸዉን ባለማወቅ የዚያን ዕለቱን የአሜሪካን የሬዲዮ ፕሮግራም ዝግጅት ማዳመጤ እነሆ ጩጉዋራየን እየላጠዉ ይገኛል። እጅግ በጣም ያሳፍራላ!! ይሁን እንጂ ከዚያች ዕለት

ጀምሮ በህሊናየ የሚመላለሰዉን ጥያቄ አንባቢዎች (ምናልባት) አስተያየት ሊሰጡበት ይችሉ ዘንድ ወይም ደግሞ ምን ያህል በእኔ የተፈጠረዉ ስሜት በሌላዉም ኢትዮጵያዊ እንዳለ ማወቅ እችል ዘንድ ሃሳቤን ማቅረብ ወደድሁ።

ለመሆኑ የዚችን ዉብ ሃገራችንን እንዲሁም የምስኪን ህዝባችንን የወደፊት እጣ ፋንታ ለእነኝህ አይነት የሃገር መሪ ተብየዎች ለምን ያህል ጊዜ አሳልፈን መስጠት እንፈልጋለን? ስንቶቻችንስ እንሆን በተቃራኒዉ እንዲህ አይነቱ ጉዳይና አሳፋሪ ሁኔታ እምብዛም ስሜት አልሰጥ ብሎን መልካም እንቅልፍ ተኝተን የምናድር? ስንቶች በዉጭ ሃገር የምንገኝ ኢትዮጵያዊያን እንሆን በአሁኑ ሰዓት አገራችን ያለችበትን አሳሳቢ ችግር ችላ ብለን አሁንም በንብረት ላይ ንብረት በማፍራት አገር ቤት ዉስጥ ‘ኢንቨስት’ ለማድረግ ደፋ ቀና እያልን ከዚህ አሳፋሪ መንግስት ጋር መሞዳሞዳችንን በመቀጠል ላይ ያለን? ከዚህ በተቃራኒዉስ ስንቶቻችን እንሆን ይህና ተመሳሳይ የሃገራችን ችግሮች ከማሳሰብ አልፈዉብን  ችግሮችን ለመቅረፍ እየተደረገ ባለው ተግባራዊ እንቅስቃሴ ዉስጥ ተሳታፊ ሆነን የምንገኝ?

ኢትዮጵያዊያን ወንድሞቸ! ዛሬ በአገራችን የሚገኘዉ ምስኪን ህዝብ እየደረሰበት ያለዉ ብሶትና ግፍ ከማንገሽገሽ አልፎ ‘ማስመለስ’ ከጀመረዉ ቆይቱዋል። ይህ ምስኪን ህዝብ ይህን ግፍና በደልም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከትከሻዉ ላይ አሽቀንጥሮና ወርዉሮ ለመጣል የሁኔታዎችን አመቺነት እየተጠባበቀ ይገኛል፡ ለዚህም ምንም አይነት ጥርጣሬ የለኝም። ይሁን እንጂ ከዚህ ብሶትና ግፍ ለመላቀቅ በዉስጡ ያለዉ ስሜትና አንዳንዴም ከልክ ሲያልፍበት የሚያደርገዉ የአልገዛም ባይነት እንቅስቃሴ እጅግ በሚገርም በሚያሳዝንና  በሚዘገንን ሁኔታ አፈና እየተደረገበት ይገኛል። ለዚህም አፈና ዎጤታማነት ለወያኔ ጥቅም ያደሩ ‘የወገን’ ሆዳሞች ትብብር ከፍተኛውን ሚና የሚጫወት ሲሆን ከዚህ በተረፈ ደግሞ ራሱ ወያኔ በጉልበት እያካሄደ ያለው ነገር ግን የማያዛልቅ አገዛዝ ተጠቃሾች ናቸው። ነገር ግን ተወደደም ተጠላ በዚህ ህበረተሰብ ዉስጥ ያለዉና እየተንተከተከ የሚገኘዉ ስሜት ትንሽዬ መዉጪያ ቀዳዳ ማግኘትን የሚፈልግ ሲሆን ያች ‘ትንሽዬ ቀዳዳ’ የተገኘች ዕለት ....... ይብላኝ ለወያኔና ለጭፍረኞቹ!

ታዲያ ይህች ‘ትንሽዬ ቀዳዳ’ እንዴት ትፈጠር?  በአሁኑዋስ ወሳኝ ሰዓት ማንና በምንስ አይነት መልክ ለዚች ‘ትንሽዬ ቀዳዳ’ መፈጠር ሚና ይጫወት? የሚሉና በጣም ቀላል የሚመስሉ ነገር ግን ዉስብስብ የሆኑ ጥያቄዎች ይገጥሙኛል። በኔ የግል አመለካከት (በአሁንዋ ወሳኝ ሰዓት) ለእነኝህ ጥያቄዎች መልስ ፍለጋ ፊቴን የማዞረዉ በዉጭ ሃገር ወደ አለዉና በተለያዩ ምክንያቶች ከእናት ሃገሩ ርቆ በስደት ወደሚገኘዉ በሚሊዮን የሚቆጠር ኢትዮጵያዊ ህብረተሰብ ነዉ።

ወገኖቸ! እነሆ ኢህአዴግ እንደ አቦይ ‘ስጠጣ ነጋ’ን አይነት ፍጥረቶች አሰባስቦ የስልጣን ወምበሩን ከተቆናጠጠ ጀምሮ ባሉት በርካታ ዓመታት

- በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ንጹሃን ወንድሞቻችን፡ እህቶቻችን፡ አባቶቻችን፡ እናቶቻችን፡ልጆቻችን ይህም ካልሆነ ዘመዶቻችንና ጉዋደኞቻችን በአደባባይና በሚስጥር ተገደሉ፡ አለቁ። ይህ ሲሆን ስንቶቻን እንሆን በቁጭት የተንገበገብን? ከዚህም አልፎ ምን ማድረግ እንድሚገባን ያሰብንና የወሰንን? ስንቶቻችንስ እንሆን ይህ ግፍና በደል ተረስቶን ለግል ህይወታችን ብቻ ትኩረት በመስጠት ለግል ኑሮአችን ብቻ ደፋ ቀና እያልን የምንገኝ?

- በብዙ ሽህ የሚቆጠሩ ንጹሃን ወንድሞቻችን፡ እህቶቻችን፡ አባቶቻችን፡ እናቶቻችን፡ልጆቻችን ይህም ካልሆነ ዘመዶቻችንና ጉዋደኞቻችን  በተለያዩ የአደባባይና የሚስጥር እስር ቤቶች ዉስጥ ታጉረው ፍዳቸዉን ቆጠሩ፡ እየቆጠሩም ይገኛሉ። ይህ ሲሆን ስንቶቻን እንሆን በቁጭት የተንገበገብን? ከዚህም አልፎ ምን ማድረግ እንድሚገባን ያሰብንና የወሰንን?

- በአሁኑዋ ሰዓት አገራችንና የሃገራችን ህዝብ በክልል ዞን ወረዳ ጎጥና መንደር በዘርና በጎሳ በመከፋፈሉ ምክኒያት ቀደም ብሎ በሰላምና በወንድማማችነት ይኖር የነበረዉ ህዝብ እርስ በርሱ እየተጋጨና ቀደም ብሎም ወደነበረበት ሁኔታ ለመመለስ አስቸጋሪና ፈታኝ ወደ ሆነ ደረጃ ላይ ደርሶአል። እነአቦይ ‘ስበላ ነጋ’ በንቀት ይህን ተግባር ሲፈጽሙብን ስንቶቻን እንሆን በቁጭት የተንገበገብን? ከዚህም አልፎ ምን ማድረግ እንድሚገባን ያሰብንና የወሰንን?

- ትናንት በጠፍር ጫማና ‘ባስራሰባት መርፌ በተጠቀመ’ ቁምጣ ስልጥን ላይ የወጡት የዛሬዎቹ ‘ጌቶቻችንና ጭፍሮቻቸዉ’ የሃገራችንን አንጡራ ሃብት ያለምንም ገደብና ‘ሃይ ባይ’ ዘርፈዉ በአገሪቱ አሉ የሚባሉት ሃብታሞች እነሱ ብቻ ሆነዋል። ይህስ ሲሆን ስንቶቻችን እንሆን ከወሬ ባሻገር ተግባራዊ የሆነ አስተዋጾ በማድርግ ይህን በየትኛዉም አገር ታሪክ ታይቶ የማይታወቅ  ‘ካንሰር’ አይነት የሆነ መንግስት ከስሩ መንግለን ለመጣል ወስነን የተነሳን?

- ይህ መንግስት አገራችንን ያለወደብ ከማስቀረት አልፎ በተለያዩ አቅጣጫዎች የሃገራችንን መሬት እንደጨርቅ እየቆራረጠና መሃል አገር ያሉትንም በርካታ የልማት ቦታዎች ‘ለዉጭ ሃገር ባለሃብቶች’ ሲቸበችብ ይህ ተግባር አሁን ላለነዉ ብቻ ሳይሆን ለልጆቻችንና ለልጅ ልጆቻችን የሚያተርፈዉ ጦስ አሳስቦን ችግሩ ተባብሶ መመለስ ከማይችልበት ደረጃ ከመድረሱ በፊት የምንችለዉንና የየአቅማችንን ለማድረግ ወስነን የተነሳን?

- እጂግ በርካታ የሆንን ኢትዮጵያዊያን ዜጎች የዚህ ግፈኛ መንግስት ቀጥተኛ ሰለባ ላለመሆን ስንል በተለያዩ የዓለማችን ክፍሎች በስደት ተበታትነን እንገኛለን። ይህ የስደት ኑሮ አንገብግቦንና አሳስቦን ባለንባቸዉ ሃገራት ያለንን በነጻነት የመንቀሳቀስ መብት በመጠቀም በሃገራችን ያለዉን አስከፊ ሁኔታ ለዓለም ህዝቦች በማሳወቅ ላይ የምንገኝ ስንቶቻችን እንሆን?

- ኢህአዴግ ይህችን አገር እንዳልነበረች ለማድረግ ሲያደርግ የቆየዉና እያደረገ ያለዉ ተግባር እንዲህ በአጭሩ ተገልጾ እንዴትስ ሊያበቃ ይችላል? ከላይ የተጠቀሱትን ለአብነት ከወሰድን በቂ አይመስላችሁም? ታዲያ እንደ አንድ ኢትዮጵያዊ ዜጋ ምን ማድረግ ይገባናል ብላችሁ ታስባላችሁ? ወይንስ አሁንም ችግሮቹ እንደማይመለከቱት ሰዉ ነገሮችን በዝምታ ማየትን እንመርጣለን? ዉድ ኢትዮጵያዊያን ወንድሞቸ! ለእኔ የዚህ ‘ዝምታ’ ሚስጥር ባይገባኝም የኢትዮጵያና ኢትዮጵያዊያን ችግር እጂግ አሳሳቢ ደረጃ ላይ መድረሱ ግን ከመቼዉም ጊዜ በላይ አሳስቦኛል።

ቀደም ብየ ለመግለጽ እንደሞከርሁት (በአሁኑዋ ወሳኝ ወቅት) ኢትዮጵያና የኢትዮጵያ ህዝብ የገጠሙዋቸዉን ከባድና ዉስብስብ ችግሮች ለመቅረፍና ‘ትንሽየዋን ቀዳዳ’ ለመፍጠር የተሻለ ዕድል ያለዉ በዉጭ ሃገር በስደት ላይ የሚገኘው ህብረተሰብ ይመስለኛል። ለዚህም አመለካከቴ ዋና መሰረቱ በዉጭ ሃገር የሚገኘዉ ኢትዮጵያዊ ህብረተሰብ በሃገር ዉስጥ ከሚገኘዉ ህዝብ እጅግ የላቀ በነጻነት የመንቀሳቀስ የኢኮኖሚም አቅም አለዉ የሚለዉ እምነቴ ነዉ።

ይሁን እንጅ እስከአሁን ያለው በዉጭ ሃገር የሚገኙት ኢትዮጵያዊያን ተሳትፎ ምን ያህል ነው?ምንስ ይመስላል? ብለን ራሳችንን ብንጠይቅ ምላሹ ለሁላችንም ግልጽ ይመስለኛል። ምንም እንኩዋን ከቅርብ ጊዜ ወዲህ እየተፋፋመ የመጣዉ እንቅስቃሴ አበረታች ቢሆንም በዉጭ ሃገር ከሚገኘዉ ኢትዮጵያዊ ስደተኛ ቁጥር አንጻር ሲታይ በሃገራችን ላይ በአሁኑ ሰዓት እየታየ ላለዉ አሳሳቢ ችግር መፍትሄ ለመፈለግ ቁርጠኛ ዉሳኔ አድርገዉ ወደትግሉ ሜዳ የገቡት ግለሰቦች ቁጥር በጣም አነስተኛ እንደሆነ የምንስማማ ይመስለኛል።

እዚህ ላይ ነዉ እንግዲህ እጅግ በጣም የሚያሳስቡኝን ጥያቄዎች ማቅረብ የምፈልገዉ። ለመሆኑ ይህ ዝምታ ጤናማ ነዉ ወይ? ይህ ዝምታ እስከየትስ ድረስ ይወስደናል? በሃገራችን ሊደርስ የሚችለዉ አስፈሪ ጥፋት አያሳስበንም ወይ? እያንዳንዳችን ቢያንስ እጅግ የቀረበ ዘመዳችን ቢበዛ ደግሞ የሩቅ ዘመድ ወይም ጉዋደኛችን ከላይ ከዘረዘርሁዋቸዉ በደሎች ዉስጥ ቢያንስ የአንደኛዉ ግፍ ሰለባ ለመሆኑ ምንም የሚያጠራጥር ነገር በሌለበት ሁኔታ የዝምታችን መንሳኤ ምን ይሆን?የሚሉትን ማለት ነው።

ታዲያ የእያንዳንዳችንን በር እያንኩዋኩዋ ያለዉን ችግር አብዛኞቻችን እንደ አንድ የዉጭ ሃገርና የማይመለከተዉ ዜጋ እጃችንን አጣጥፈን በትዝብት የምንመለከትበት ምክንያት ምን ይሆን? ማንስ ከዚህ አሳሳቢ ችግር እንዲያላቅቀን እናስባለን? እንፈልጋለን?

እስኪ ከላይ ያነሳሁዋቸዉን ጥያቄዎች ለአንድ አፍታ ራሳችንን እንጠይቅ። መጠየቅ ብቻም ሳይሆን ምን ማድረግ እንደሚገባን እናስብ፡ ማሰብ ብቻም አይደለም ምንም አይነት ጊዜ ሳናጠፋ ይህችን ሃገራችንንና ይህን ምስኪን ህዝብ ከዚህ ደም መጣጭ መዥገር መንግስትና እንደ እነ አቦይ ስብሃት ነጋ አይነት አጥፊ የሆኑ ፍጥረታት ለማላቀቅ ዛሬዉኑ መንቀሳቀስ እንጀምር። በጣም በሚያበረታታና አዲስ ተስፋን በሚፈነጥቅ ሁኔታ እየተንቀሳቀሱ ያሉ ተቃዋሚ ሃይላትንም አይዞአችሁ እኛም ከጎናችሁ ነን እንበላቸዉ።

ሁላችንም በስፋት እንደምናውቀዉ በአሁኑ ሰዓት በርካታ የሆኑ የተለያዩ ይሁን እንጂ ይህን ዘረኛ መንግስት ከማስወገድ አንጻር ሲታዩ አንድ አቋዋም ያላቸዉ የዚህ ግፈኛ መንግስት ተቃዋሚ ድርጅቶችና ቡድኖች ስላሉ ከእነኝህ ድርጅቶች ወይም ቡድኖች ዉስጥ ትክክለኛ አካሄድን እየተከተለ ነዉ፡ በአሁኑ ወቅት በአገራችን ህብረተሰብ ላለዉ አስከፊ ችግር የተሻል መፍትሄ ሊያመጣ ይችላል ብለን የምናምንበትን አንዱን ዛሬዉኑ በመቀላቀል የዜግነት ድርሻችንን እናበርክት፡ ይህችን ሃገርና ምስኪን ህዝባችንን ከጥፋት እንታደግ፡ ‘ዝምታዉ ይሰበር‘ በማለት ጽሁፌን አጠቃልላለሁ።

‘ዝምታዉ ይሰበር‘ እኛም ቸር እንሰንብት።

www.ethiomedia.com – a site of alternative news and views